የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ

# የ **2011** በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

**ሐምሌ 2011 ዓ.ም.**

አዲስ አበባ

ማውጫ

1. አጭር ማጠቃለያ............................................................................................... 2
2. የዝግጅት ምዕራፍ............................................................................................... 3
3. የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት.............................................................................. 4
3.1. የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ.......................................................................4
3.2. ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለን መስተጋብር ማጎልበት.....................................4
3.3. የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድን ማሳደግ.........................................................................7
3.3.1. ወጪ ቆጣቢነትንና ውጤታማነትን ማሻሻል..................................................7
3.3.2. የክልሎችና ጤና ተቋማት የመድሃኒት በጀት አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት........................10
3.3.3. የመድኃኒት ብክነት መቀነሻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ........................................12
3.3.4. የመድሃኒት ዋጋ ትመና ማጠናከር.............................................................13
3.3.5. ገበያ ጥናት በማከናወን ገበያውን ማረጋጋት.................................................13
3.4. የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን ማጎልበት...........................................14
3.4.1. ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ማጠናከር.........................................................14
3.4.2. የግዥ ጨረታ አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር...................................................15
3.4.3. የሀገር ውስጥ አምራቾች አፈጻጸም.............................................................17
3.4.4. የኮንትራት አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር......................................................21
3.4.5. የመጋዘን አያያዝና የክምችት አስተዳደር ሥርዓት ማጠናከር.......................................22
3.4.6. የስርጭት እና ተሽከርካሪዎች ስምሪት አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር...............................24
3.5. ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት.............................................................................26
3.5.1. የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ማጎልበት......................................................26
3.5.2. የአቅርቦት ሰንሰለት መሠረተ ልማት ማጎልበት..................................................26
3.5.3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ፈጠራን ማጎልበት..........................................27
3.5.4. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጎልበት.........................................................28
3.5.5. የመድሃኒት አቅርቦት ለማረጋገጥ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር......................................29
3.5.5.1. የመልካም አስተዳደር እና ስነምግባር አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር..........................29
3.5.5.2. የህግ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር.....................................................30
3.5.5.3. ስርዓተ ጾታ እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ አገልግሎት ማጠናከር..........30
4. የበጀት ዓመቱ የፋይናንስ አጠቃቀም.............................................................................. 31
5. በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች.............................................................................. 32

## 1. አጭር ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ እየተተገበረ የሚገኘውን የአምስት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የግማሽ ዘመን አፈፃፀም ግምገማ በማድረግ ዕቅዱን ከልሶ አዘጋጅቷል። ስትራቴጂክ ግቦቹን ለክትትልና ግምገማ በሚያመች መልኩ ተዘጋጅቷል። የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ከተከለሰው ስትራቴጂክ ዕቅድ የተቀዳ ሲሆን እንደ ፍላግሺፕ ስትራቴጂክ እርምጃ የህይወት አድንና የመሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦትን ከ65% ወደ 95% ለማድረስ ታቅዷል።

የዕቅድ አፈጻጸሙን ለመከታተል የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎችን በኤጀንሲ ደረጃ (Corporate level KPIs)፣ በስራ ሂደት ደረጃ (Process level KPIs) እና ለእያንዳንዱ ፈጻሚ (individual level KPIs) ተዘጋጅቷል። የዕቅድ አፈጻጸሙን በአፈጻጸም መለኪያዎች ለመለካት እንዲቻል የመረጃ መሰብሰቢያ እና ሪፖርት ማድረጊያ ቅፆች ተዘጋጅተው ወደ ተግባር ተገብቷል። እንዲሁም በአዳማና በደሴ ቅርንጫፎች የክትትልና ግምገማ ትግበራ ሜንተርሽፕ የተሰጠ ሲሆን የቅርንጫፍ ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎች ወጥ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም የጤና ተቋማት (የደንበኞች) እና የሰራተኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት የጤና ተቋማትና የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ለመስራት የሚያስችሉ ቱሎች ተዘጋጅተው በአዳማ ቅርንጫፍ የሙከራ ዳሰሳ የተካሄደ ሲሆን በሙከራ ዳሰሳው ውጤት መሰረትም ቱሎችን ሊያሰሩ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጓል። እንዲሁም ከቅርንጫፎች እና ከዋናው መስሪያቤት ለተውጣጡ 93 ስራ አስኪያጆች እና አስተባባሪዎች ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት ስልጠና ማለትም በመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና ትንተና ዙሪያ በሶፍትዌር (Statistical Package for Social Science) በመጠቀም ሰልጣኞች መረጃ ለመተንተንና የዳሰሳ ጥናት ውጤቱን ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችላቸውን በተግባር የታገዘ በሁለት ዙር ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ የጤና ተቋማት እርካታ 75% ሲሆን የሰራተኞች እርካታ 58% ነው።

የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት (Forecast Accuracy) ለጤና ፕሮግራም ግብአቶች የትንበያ ትክክለኛነት በአማካይ 82.78% ሲሆን ለተመረጡ የተገላባጭ ፈንድ መድኃኒቶች የትንበያ ትክክለኛነት 62.3% ነው።

የህይወት አድንና የመሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦትን ከ69% ወደ 95% ማድረስ የታቀደ ሲሆን አፈጻጸም በመደበኛ ፕሮግራም 90.7% እንዲሁም በጤና ፕሮግራም 95% ነው። በበጀት ዓመቱ ውስጥ የነበረው የበጀት አጠቃቀም 57% ነው።

## 2. የዝግጅት ምዕራፍ

የኤጀንሲውን የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ለመገምገም ከባለድርሻ አካላት ጋር የ3 ቀናት የግምገማ መድረክ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በግምገማ መድረኩ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ዘርፍ ቋሚ ኮሚቴ፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከሆስፒታሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተሳተፉበት ተካሂዷል። በመድረኩ ላይም የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና የ2011 በጀት ዓመት አንኳር ዕቅድ ቀርበው ውይይት ተደርጎበታል። የ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በየደረጃው በማካሄድ ለ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ በግብዓትነት ተወስደዋል። የ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ ኤጀንሲውን በበለጠ ሊገልጹና ሊለኩ የሚችሉ ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ ግቦች ተቀርጸዋል። እነዚህን የኤጀንሲው ስትራጂክ የትኩረት መስኮችና ስትራቴጂክ ግቦች በየደረጃው የሚገኝ አመራር እንዲረዳው በማድረግ የኤጀንሲውና የስራ ክፍሎች ዕቅድ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም ለፈጻሚዎች ኦሬንቴሽን ተሰጥቶ ዕቅዱ በየደረጃው ከወረደ በኋላ ወደ ተግባር የተገባ ሲሆን ዕቅዱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ተልኳል።

የክትትልና ግምገማ የስልጠና ማኑዋል ተዘጋጅቶ የአሰልጣኞች ስልጠና በሁለት ዙር ከሁሉም ቅርንጫፍ ለተውጣጡ 124 አስተባባሪዎች ተሰጥቷል። እንዲሁም በዋናው መስሪያ ቤትና በሁሉም ቅርንጫፎች ለሚገኙ 52 አዳዲስ የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ባለሙያዎች እና ለቅርንጫፍ ምክትል ስራአስኪያጆች በመሰረታዊ የክትትልና ግምገማ እንዲሁም በአፈጻጸም መለኪያዎች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል። የኤጀንሲው የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። የኤጀንሲውን፣ የስራ ክፍሎችንና ፈጻሚዎችን ለመለካት የሚያስችሉ ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች በማዕቀፉ ተካተዋል። የክትትልና ግምገማ ማዕቀፉ ኤጀንሲው ባዘጋጀው ዓመታዊ የግምገማ መድረክ ላይ በይፋ ተመርቆ ወደ ስራ ተገብቷል።

## 3. የ 2011 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ የ2011 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በቁልፍና አበይት ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1. የጤና ልማት ሠራዊት እንቅስቃሴ

በኤጀንሲው 162 የኬዝ ቲም ፎረሞች ያሉ ሲሆን በዋናው መ/ቤት 40 ኬዝ ቲም ፎረም እና በቅርንጫፍ ደረጃ 122 ኬዝ ቲሞች ተደራጅቷል። በዋና መ/ቤት የኬዝ ቲም ፎረሞች ግንኙነት እና ውይይቶችን በተመለከተ

ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እያጣጣሙ ከማካሄድ አንጻር የዳሰሳ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት የጤና ልማት ሰራዊት ውጤታማ እንዳይሆን የሚያደረጉት ክፍተቶች ተለይተው ክፍተቱን ለመሙላት እና ሰራተኞችን በማነቃቃት የማስፈፀም አቅማቸውን መጨመር እንዲቻል የጥራት ትስስር የአሰራር ስርዓት (Quality circle manual) ለመተግበርና በሲስተም የታገዘ ለማድረግ ማንዋል ተዘጋጅቷል።

## 3.2. ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለን መስተጋብር ማጎልበት

የስትራቴጂክ እርምጃዎች አፈጻጸም

የመድኃኒት አቅርቦቱን ከማሻሻል አንፃር የፈጣን ለውጥ አምጪ ስልትን በመቀየስ 74 ስፔሻላይዝድና ከፍተኛ የታካሚ ብዛት ያላቸውን ሆስፒታሎች በመለየት የክምችት ክትትል ስራዎች ተሰርተዋል፤ በዚህም አጠቃላይ የመድሃኒት ግኝት ከ 90 በላይ ሆኗል። ከመድኃኒትና የህክምና መገልገያ አቅራቢዎችና ወኪሎች ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር ከ 64 የአቅራቢዎች ወኪሎች ጋር በአቅርቦት ዙሪያ እና ወደፊት ለሚኖረው የስራ አፈፃፀም መለኪያዎች (KPIs) ላይ ውይይት በማድረግ አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል።


ነጻ የስልክ መስመር 8772 ለማዘመን ወደ ዲጅታል E1 በመቀየር እንዲሁም ዞይፐር የተባለ ሶፍትዌር በመጠቀም በተመሳሳይ ሰዓት ሁለት ሰዎች ብቻ ሲያስተናግድ የነበረውን ተጨማሪ 30 መስመሮች በመጨመር ተደራሽነቱን የማስፋት ስራ ተሰርቷል። ከዚህም በተጨማሪ የነጻ ስልክ መስመሩ አጭር የጽሁፍ መልዕክት በማስተላለፍ ይገኛል። በበጀት ዓመቱ በነጻ የስልክ መስመሩ በተለያዩ ጤና ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች ለቀረቡ ጥቆማዎች እና አስተያየቶች በአግባቡ ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። እንዲሁም የሚዲያ ፎረም ወርክሾፕ ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋር በመድኃኒት አቅርቦት ዙሪያ ውይይት የተደረገ ሲሆን በተለያዩ ሚዲያዎች በመድኃኒት አቅርቦት ዙሪያ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል።

በኤጀንሲ በየደረጃው ያለውን የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት በማጠናከር እንዲሁም አግባብ ያለው የግብረ መልስ አሰጣጥ ስርዓት በማጎልበት የክምችትና ስርጭት ስርዓቱን በማሻሻል በክምችት ያሉ መድሃኒቶች በተገቢው ሁኔታ ለህብረተሰቡ ማድረስ ያስችል ዘንድ አዳዲስ ወደ ክምችት የሚገቡ መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎችን በማህበራዊ ሚዲያ (በቫይበርና በቴሌግራም) የማሳወቅ ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ጉዳዮች በማህበራዊ ሚዲያ ለማስተዋወቅ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በኤጀንሲው የፌስቡክ ገጽ ላይ ሊንክ በመጫን የመድሃኒቶች አቅርቦት መረጃዎችን ለተገልጋዮች ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም በፌስቡክ 169 እና በቲውተር ገፅ 88 ዜናዎችን እና መረጃዎችን በማዘጋጀት በኤጀንሲው ማህበራዊ ድረ-ገፅ ማሰራጨት ተችሏል።


የኤጀንሲው የኮሙንኬሽን ስትራቴጂ የተዘጋጀ ሲሆን ለኮሙንኬሽን ስትራቴጂው አጋዥ የሆኑ ቁልፍ የአፈጻፀም መለኪያዎችና የአሰራር መመሪያዎች (SOPs) እንዲሁም ከኮሙንኬሽን ስትራቴጂው የተቀዳ የአንድ ዓመት እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል። ተቋሙን አስመልክቶ የህብረተሰቡን እና የሰራተኛውን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የተለያዩ የኮሙንኬሽን ስራዎች ተከናውነዋል። ከነዚህም ውስጥ በሁለት ቋንቋ የተዘጋጀ 1000 ኮፒ መጽሄት ታትሞ

ለተለያዩ አካላት ተሰራጭቷል። የኤጀንሲውን ስያሜና ሎጎ የማሳተምና የማስተዋወቅ ስራ፣ ኤጀንሲው ከያዛቸው ፍላግሽፕ ኢንሸቲቭ አንዱ የሆነውን “መድሃኒት የለም ይቁም“ (“STOP STOCK OUT”) የሚለውን መልዕክት በመቅረጽ ሁሉም ሰራተኛ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ  ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም በኤጀንሲው ያለውን የኢሜል ልውውጥ አንድ ወጥ ለማድረግ እንዲያስችል የተቋም ኢሜል (Corporate email) ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል።

የሰራተኞችን ተነሳሽነት ለመጨመር እና ኤጀንሲው እየሰራ ያሉትን ስራዎች እንዲያውቁ ለማድረግ በአዳማ ቅርንጫፍ እየተሰሩ ያሉትን የለውጥ ጅማሬዎቸ ሁሉም የዋና መስሪያ ቤት እንዲሁም የአዲስ አበባ ቁጥር 1 እና 2 ሰራተኞች እንዲጎበኙ ተደርጓል። የጤና ተቋማት (የደንበኞች) እና የሰራተኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት የጤና ተቋማትና የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ለመስራት የሚያስችሉ ቱሎች ተዘጋጅተው በአዳማ ቅርንጫፍ የሙከራ ዳሰሳ የተካሄደ ሲሆን በሙከራ ዳሰሳው ውጤት መሰረትም ቱሎችን ሊያሰሩ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጓል። እንዲሁም ከቅርንጫፎች እና ከዋናው መስሪያቤት ለተውጣጡ 93 ስራ አስኪያጆች እና አስተባባሪዎች ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት ስልጠና ማለትም በመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና ትንተና ዙሪያ በሶፍትዌር (Statistical Package for Social Science) በመጠቀም ሰልጣኞች መረጃ ለመተንተንና የዳሰሳ ጥናት ውጤቱን ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችላቸውን በተግባር የታገዘ በሁለት ዙር ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ዳሰሳ ጥናት ተካሂዶ የጤና ተቋማት እርካታ 75% ሲሆን  የሰራተኞች እርካታ 58% ነው።




**ምስል 1፡** የመድኃኒት አቅራቢ ኤጀንሲ የሰራተኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ውጤት




ምስል **2**፡ የጤና ተቋማት የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ውጤት

የአፈጻጸም መለኪያ

**KPI1:** የጤና ተቋማት እርካታ ወደ 80% ማድረስ- አፈጻጸም- 75% ነው::

## **3.3.** የተገላባጭ መድሃኒት ፈንድን ማሳደግ

ስትራቴጂክ እርምጃዎች

### **3.3.1.** ወጪ ቆጣቢነትንና ውጤታማነትን ማሻሻል

በበጀት ዓመቱ ወጪ በመቆጠብ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሰረት በርካታ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እና አሰራር ተዘርግቷል። በዚህም መሰረት ጊዜን እና ወጪን ለመቆጠብ በተዘረጋው አሰራር መሰረት በባህር ተጭነው የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ሞጆ ደረቅ ወደብ ከደረሱ በኋላ 51 ቀናት ይወስድ የነበረው በበጀት ዓመቱ በአማካኝ በ48 ቀናት ውስጥ ማንሳት የተቻለ ሲሆን በአየር ተጭነው የሚመጡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች በአማካኝ በ10 ቀናት ውስጥ ማንሳት ተችሏል። የኪራይ መጋዘኖችና ተሽከርካሪዎች ላይ ያለዉን ወጪ ለመቀነስ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የኪራይ መጋዘኖች ቁጥር እንዲቀንስ በማድረግ በአዳማ 1 መጋዘን እና በአዲስ አበባ 2 መጋዘኖች በድምሩ 3 መጋዘኖች ብቻ በኪራይ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪም ባለፈው አመት እና በዚህ በጀት ዓመት ከሃያ በላይ መጋዘኖች እንዲለቀቁ የተደረገ ሲሆን ለረጅም ጊዜ ተከማችተው የነበሩ የሽረት ጊዜያቸው ያለፉ መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎችን በማስወገድ የማከማቻ ቦታ እንዲኖር ተደርጓል። እንዲሁም ኤጀንሲው ለመድሃኒትና ለህክምና መገልገያዎች ስርጭት የሚጠቀምባቸውን ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ዘመናዊ ለማድረግና ለማሻሻል የሚያስችል የጂፒኤስ ተከላ በሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

## ሒሳብ መዝጋት እና የኦዲት ስራ

### በውስጥ ኦዲት የተከናወኑ ተግባራት

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በመድኃኒቶች ብልጫና ጉድለት፣ በተመረጡ ደረሰኞች ትክክለኛነት፣ የዱቤ ሽያጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩ ኦዲት እና የመድኃኒት ክምችት መጋዘኖች የመድሃኒት ክምችት ወጪ ማረጋገጫ ዙሪያ 25 የውስጥ ኦዲቶች ተከናውነዋል። ከነዚህም ውስጥ 23 የኦዲት ስራዎች ተጠናቀው የኦዲት ሪፖርት ቀርቧል:: በውስጥ ኦዲት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መከላከል ቢሮ ጥያቄ መሰረት የውሎ አበል ክፍያ ትክክለኛነት የማረጋገጥ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

2. የአዳማ ፕሮጀክት ፅ/ቤት የወጪ ሂሣብ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

3. የባህርዳር፣ የመቀሌና የነገሌ ቦረና ቅርንጫፎች፣ የዋና መስሪያ ቤት መጋዘን ቁጥር 3 እና 4 እና የኡራኤል መጋዘን የ 2009 በጀት ዓመት ብልጫና ጉድለት ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል። እንዲሁም የሽሬ ቅርንጫፍ የ 2008 በጀት ዓመት እና የ 2009 በጀት ዓመት ጉድለት እና ብልጫ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

4. የዋናው መስሪያቤት በ 2011 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የሂሳብ ክፍል የቁጥጥር ስርዓት የክዋኔ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

5. የድሬዳዋ ቅርንጫፍ የተመረጡ 10 መድሃኒቶች የ 2009 በጀት ዓመት የጉድለት እና ብልጫ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

6. የደሴ ቅርንጫፍ የመድሃኒት ጉድለት ሂሳብ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

7. የዋና መስሪያ ቤት ቃሊቲ ቁጥር 2 መጋዘን የ 2010 በጀት ዓመት የተገላባጭ ፈንድ እና የፕሮግራም መድኃኒቶች ጉድለት እና ብልጫ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

8. የዋና መስሪያ ቤት የለቡ 1 መጋዘን የ 2010 በጀት ዓመት የተገላባጭ ፈንድ እና የፕሮግራም መድኃኒቶች ጉድለት እና ብልጫ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

9. የነገሌ ቦረና ቅርንጫፍ በ 2009 እና በ 2010 በጀት ዓመት የተመረጡ ደረሰኞች ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

10.የዋናው መ/ቤት ከሐምሌ 1 ቀን 2010 እስከ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ያለው የየወሩ የመድኃኒት ክምችት መጋዘኖች የመድሃኒት ክምችት ወጪ ማረጋገጫ (Dispatch confirmation) እና የጤና ተቋማት የክምችት ርክክብ ማረጋገጫ (ሞዴል-19 confirmation) ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

11.የባህርዳር ቅርንጫፍ ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም. የመድሃኒት ክምችት መጋዘኖች የክምችት ወጪ ማረጋገጫ (Dispatch confirmation) እና የጤና ተቋማት የክምችት ርክክብ ማረጋገጫ (ሞዴል-19 confirmation) ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

12.የድሬደዋ ቅርንጫፍ ከሐምሌ ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ ጥቅምት 15 ቀን 2011 ዓ.ም. የመድሃኒት ክምችት መጋዘኖች የክምችት ወጪ ማረጋገጫ (Dispatch confirmation) እና የጤና ተቋማት የክምችት ርክክብ ማረጋገጫ (ሞዴል-19 confirmation) ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

13.በአዲስ አበባ ቁጥር-1 ቅርንጫፍ በተመረጡ መድኃኒቶች ላይ ለየካቲት 12 እና ለራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታሎች በዱቤ የተሸጡ መድኃኒቶች በትክክል ገቢ መሆናቸውን ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

14.በተመረጡ አርባ ከፍተኛ የሽያጭ እንቅስቃሴ ያላቸውን የተገላባጭ ፈንድ መድኃኒቶች ክምችትና ስርጭት ለግል ተቋማት የሽያጭ ክዋኔ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

15.በአየር የተጓጓዙ ጭነቶች መጋዘን ለመድረስ የወሰደው ጊዜ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

16.በጅማ ቅርንጫፍ ለሆራይዘን ፕላንቴሽን አክስዮን የግል ማህበር ሊሙ ቡና እርሻ ልማት ከ2006-2008 ዓ.ም. የተካሄደውን የዱቤ ሽያጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

17.በተመረጡ መድሃኒቶች ከዋናው መ/ቤት ወደ ድሬደዋ ቅርንጫፍ መጋዘን ተልከው ገቢ የተደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ልዩ ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል። እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቁጥር-1 ቅርንጫፍ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተልከው ገቢ የተደረጉ መድኃኒቶች ኦዲት ተጠናቆ ሪፖርት ቀርቧል።

18.የሰመራ ቅርንጫፍ የ2009 በጀት ዓመት እና የ2010 በጀት ዓመት ጉድለት እና ብልጫ ሂሳብ ኦዲት በሂደት ላይ ይገኛል።

19.የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ቁጥር-1 የ2009 በጀት ዓመት ጉድለት እና ብልጫ ኦዲት እየተከናወነ ይገኛል።

<u>በውጭ ኦዲት የተከናወኑ</u>

ባለፉት ዓመታት የኤጀንሲው ሂሳብ በፋይናንስ አዋጁ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አለመዝጋት፣ ኦዲት አለማስደረግ እና በሚሰጡ የኦዲት አስተያየቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድ ክፍተቶች ነበሩበት። በአሁኑ ወቅት፡-

1. የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተጠናቆ የኦዲት ሪፖርት በመጠበቅ ላይ ይገኛል።
2. የ2010 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት ተጠናቋል።

ከዚህ በፊት በከፍተኛ ደረጃ የስጋት ምንጭ የነበረው የኦዲት ውዝፍ በዚህ አመት ተጠናቋል።

<u>የፋይናንስ ውስጣዊ አሰራር ለማጠናከር የተከናወኑ ተግባራት</u>

የሞዴል 19 የአሰባሰብ ስርዓቱን በማጠናከር ወጥ የሆነ ፎርማት አዘጋጅቶ በመላክ እና ሞዴል 19 በወቅቱ የማይሰጡትን ተቋማት በመለየት ሞዴል 19 በአግባቡና በወቅቱ እየተሰበሰበ ይገኛል። በሲስተም እና በቆጠራ መካከል ያለውን ልዩነት ማጥራትና ወቅቱን የጠበቀ የሂሳብ ልዩነትን የማስታረቅ ስራ ተሰርቷል።

በቅርንጫፎችና ዋናዉ መስሪያቤት መካከል ያለዉን የሂሳብ ልዩነት ለማጥቡብ የተለያየ ግብረ-ሃይል በማቋቋም ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ የሚከታተል ባለሙያ በመመደብና ውይይት በማድረግ በቅርንጫፎች የሂሳብ ልዩነት ለማጥቡብ እንዲያስችል የመስክ ምልከታ የተደረገ ሲሆን በመስክ ምልከታዉ በታዩ ለሂሳብ ልዩነት እንደ ምክንያት የሆኑትን ስራዎች ለማስተካከል እንዲቻል ቻርትኦፍአካዉንት የመከለስ እና አዉቶኢምፖርት በማድረግ የማሻሻል ስራ እየተሰራ ይገኛል።

አለም አቀፍ ደረጃ ያለው የሂሳብ ሪፖርት (IFRS) ተግባራዊ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ከተባበሩት መንግስታት የስነ-ህዝብ ፈንድ ጽ/ቤት (UNFPA) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ለዋና መስሪያቤት እና ለቅርንጫፍ የፋይናንስ ሰራተኞች የ IFRS ስታንዳርድ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

የተገላባጭ ፈንድ መጠንን ለመጨመር የተከናወኑ ተግባራት፡-

- ኤጀንሲው ቀደም ሲል የተጠናከረ የበጀት ስርዓት ያልነበረው ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት በጥናት ላይ የተመሰረተ በጀት እንዲዘጋጅ እና እያንዳንዱ ስራ የተያዘለትን በጀት ተከትሎ እንዲፈጸም ተደርጓል።
- የተመደበውን በጀት ለመከታተል እንዲቻል እና ወጪ የሚያንሩ አሰራሮች እና የስራ ክፍሎች በመለየት ማስተካከያ እርምት መውሰድ እንዲቻል Management Accounting Team በማቋቋም የተጠናከረ ስራ እየተሰራ ይገኛል።
- በበጀት ዓመቱ ወጪ ለመቀነስ ኤጀንሲው ባለው ንብረት በአግባቡ እንዲጠቀም በማድረግ ከፍተኛ ወጪ ተቀንሷል።

### **3.3.2.** የክልሎችና ጤና ተቋማት የመድሃኒት በጀት አሰባሰብ ስርዓት መዘርጋት

በ2011 በጀት ዓመት ውስጥ ለጤና ተቋማት የዱቤ ሽያጭ ከሰጠው ብር 2,350,146,243.68 ውስጥ ብር 1,815,176,561.61 (77%) ተሰብስቧል። ከዚህ በተጨማሪም ከ2010 በጀት ዓመት ሳይሰበሰብ ወደ 2011 በጀት ዓመት የዞረ ያልተሰበሰበ ብር 695,154,945.33 ውስጥ ብር 397,504,867.57 (57%) ተሰብስቧል።

## በቅርንጫፎች ለጤና ተቋማት በዱቤ ከተሸጠ የተሰበሰበና ውዝፍ ሂሳብ መጠን እስከ ሰኔ **30** ቀን **2011** ዓ.ም. የሚያሣይ ሰንጠረዥ

| ቅርንጫፍ | በበጀት ዓመቱ ለጤና ተቋማት በዱቤ የተሸጠ (በብር) | በበጀት ዓመቱ ለጤና ተቋማት በዱቤ ከተሸጠው የተሰበሰበ ገንዘብ (በብር) | በበጀት ዓመቱ ለጤና ተቋማት በዱቤ ከተሸጠው የተሰብሳቢ ሂሳብ መጠን (በብር) | ከ **2010** በጀት ዓመት የዞረ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መጠን (በብር) | ከ **2010** በጀት ዓመት የዞረ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ (በብር) | ከ **2010** በጀት ዓመት የዞረ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መጠን (በብር) | በአጠቃላይ በዱቤ ከተሸጠው በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተሰበሰበ ገንዘብ (በብር) | በአጠቃላይ በዱቤ ከተሸጠው የተሰብሳቢ ሂሳብ መጠን (በብር) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አዲስ አበባ ቁጥር-1 | 823,892,712.59 | 655,986,156.87 | 167,906,555.72 | 464,096,093.76 | 274,183,587.00 | 189,912,506.76 | 930,169,743.87 | 357,819,062.48 |
| አዳማ | 131,088,517.65 | 113,829,603.82 | 17,258,913.83 | 31,898,446.89 | 1,979,751.22 | 29,918,695.67 | 115,809,355.04 | 47,177,609.50 |
| ድሬዳዋ | 108,729,379.48 | 94,041,925.79 | 14,687,453.69 | 13,128,122.86 | 11,727,273.14 | 1,400,849.72 | 105,769,198.93 | 16,088,303.41 |
| ባህርዳር | 278,162,470.36 | 187,191,319.31 | 90,971,151.05 | 66,792,808.28 | 14,851,015.06 | 51,941,793.22 | 202,042,334.37 | 142,912,944.27 |
| ደሴ | 115,426,568.26 | 103,523,904.26 | 11,902,664.00 | 21,120,564.14 | 20,681,064.14 | 439,500.00 | 124,204,968.40 | 12,342,164.00 |
| ጎንደር | 95,761,845.42 | 71,876,931.83 | 23,884,913.59 | 4,703,323.84 | 4,590,384.76 | 112,939.08 | 76,467,316.59 | 23,997,852.67 |
| መቀሌ | 87,965,632.69 | 71,143,089.24 | 16,822,543.45 | 22,090,642.82 | 12,853,666.58 | 9,236,976.24 | 83,996,755.82 | 26,059,519.69 |
| ጅማ | 115,204,328.79 | 73,274,324.10 | 41,930,004.69 | 20,347,850.65 | 12,818,012.44 | 7,529,838.21 | 86,092,336.54 | 49,459,842.90 |
| ሃዋሳ | 124,728,403.16 | 55,275,184.48 | 69,453,218.68 | 10,689,978.98 | 6,557,247.54 | 4,132,731.44 | 61,832,432.02 | 73,585,950.12 |
| ነቀምት | 73,952,226.99 | 52,778,136.13 | 21,174,090.86 | 3,739,182.95 | 3,171,324.79 | 567,858.16 | 55,949,460.92 | 21,741,949.02 |
| ጋምቤላ | 3,562,098.77 | 0 | 3,562,098.77 | 1,215,882.98 | 0 | 1,215,882.98 | 0 | 4,777,981.75 |
| አርባምንጭ | 18,833,061.27 | 10,358,081.21 | 8,474,980.06 | 10,431,073.69 | 10,268,682.38 | 162,391.31 | 20,626,763.59 | 8,637,371.37 |
| ሽሬ | 23,837,801.01 | 23,727,508.85 | 110,292.16 | 912,699.42 | 912,699.45 | -0.03 | 24,640,208.30 | 110,292.13 |
| አሶሳ | 29,245,142.29 | 27,640,594.37 | 1,604,547.92 | 2,211,954.45 | 2,211,914.17 | 40.28 | 29,852,508.54 | 1,604,588.20 |
| ነገሌቦረና | 72,459,985.07 | 64,023,880.41 | 8,436,104.66 | 6,118,810.03 | 6,118,810.03 | 0 | 70,142,690.44 | 8,436,104.66 |
| ሰመራ | 20,532,059.46 | 17,139,856.36 | 3,392,203.10 | 431,246.51 | 290,215.17 | 141,031.34 | 17,430,071.53 | 3,533,234.44 |
| አዲስ አበባ ቁጥር-2 | 180,438,996.65 | 149,810,121.39 | 30,628,875.26 | 15,226,263.08 | 14,289,219.70 | 937,043.38 | 164,099,341.09 | 31,565,918.64 |
| ቀብሪ ደሃር | 15,291,017.69 | 14,695,332.37 | 595,685.32 | 0 | 0 | 0 | 14,695,332.37 | 595,685.32 |
| ጅግጅጋ | 31,033,996.08 | 28,860,610.82 | 2,173,385.26 | 0 | 0 | 0 | 28,860,610.82 | 2,173,385.26 |
| ጠቅላላ ድምር | **2,350,146,243.68** | **1,815,176,561.61** | **534,969,682.07** | **695,154,945.33** | **397,504,867.57** | **297,650,077.76** | **2,212,681,429.18** | **832,619,759.83** |

ለጤና ተቋማት አገልግሎት ተሰጥቶ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከአጋር ድርጅቶች የአገልግሎት ክፍያ ተሰብስቧል።

| ተ.ቁ. | ዝርዝር | ከዕቃዉ ዋጋ | የግዥ አገልግሎት ክፍያ | የክምችትና ስርጭት አገልግሎት ክፍያ | አጠቃላይ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 2% | 5% | 7% |
| 1 | FMOH-MDG | 1,045,712,851.68 | 22,012,202.11 | 55,030,505.26 | 77,042,707.37 |
| 2 | FMOH-GF | 311,176,955.79 | 6,223,539.12 | 15,558,847.79 | 21,782,386.91 |
| 3 | GF-HAPCO | 1,489,639,914.02 | 29,792,798.28 | 74,481,995.70 | 104,274,793.98 |
| ጠቅላላ ድምር | | **2,846,529,721.49** | **58,028,539.51** | **145,071,348.75** | **203,099,888.26** |

በ **2011** በጀት ዓመት የተወራረደ የግዥና ስርጭት የአገልግሎት ክፍያ

ከዚህ በተጨማሪም የብር 129,248,975.94 የክምችትና የስርጭት የአገልግሎት ክፍያ የተሰበሰበ ሲሆን የብር 297,821,965.64 የአገልግሎት ቅድመ ክፍያ ለመሰብሰብ ተችሏል።

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI2:** የዱቤ ሽያጭ ተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሰብሰብ የሚወስደውን ጊዜ ወደ 60 ቀናት ማሳጠር- አፈጻጸም- አልተለካም

**KPI3:** ከአጋር ድርጅቶች ክፍያ ለመሰብሰብ የሚወስደውን ጊዜ ወደ 7 ቀናት ማሳጠር- አፈጻጸም- የግዥ አገልግሎት ቅድመ ክፍያ ለመሰብሰብ 30 ቀናት የወሰደ ሲሆን በዓይነት ወደ መጋዘን ገብተው የክምችትና ስርጭት አገልግሎት ለሰጠናቸው ክፍያ ለመሰብሰብ 60 ቀናት ወስዷል።

### 3.3.3. የመድኃኒት ብክነት መቀነሻ ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ

የክምችት አስተዳደር ስርዓቱን በማሻሻል በየደረጃው ያለውን የመድሃኒት ብክነት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ፣ የመጋዘን አስተዳደር ስርዓቱን በማሻሻል በከፍተኛ ወጪ ኤጀንሲው የተከራያቸውን መጋዘኖች ቁጥር መቀነስን እና የክምችት አስተዳደሩን በማጠናከር ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ ክምችቶችን በማዘዋወርና ክምችት የማገላበጥ ሂደቱን በማፋጠን እንዲሁም በማዕከል በብዛት የተከማቹ መድሃኒቶችንና ህክምና መገልገያዎችን ወደ ቅርንጫፍ በአደራ መልክ (Consignment) በማዘዋወር የክምችት ወጪዎችን ለመቀነስ ታቅዶ የሁሉም ቅርንጫፎች የዓመታዊ ቆጠራ ውጤት ትንተና የተሰራ ሲሆን በትንተናው መሰረት ክምቸት የሚሰጡና የሚቀበሉ ቅርንጫፎችን በመለየት 1,438 መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ተለይተው የብር 49,365,163.81 ዋጋ ያላቸው 935 መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች በማዘዋወር ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

### 3.3.4. የመድሃኒት ዋጋ ትመና ማጠናከር

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI4:** ለመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ዋጋ ለመትከል የሚፈጀውን ጊዜ /Average Time from GRNF to Cost set date (IGRV-GRV) ወደ 1 ቀን ማሳጠር - አፈጻጸም- 1 ቀን ነው።

### 3.3.5. ገበያ ጥናት በማከናወን ገበያውን ማረጋጋት

የአቅርቦት ፍላጎትን ለማሟላት የትንበያ ስርዓቱንና የገበያ ጥናት አቅማችንን ማጎልበት ሲሆን በዚህም መሰረት በማድረግ የገበያ ጥናት ልምዶችን የመቅሰም እና የድርጅቶችን ልምድ በመውሰድ የገበያ ጥናት ቡድን ተቋቁሞ በመስራት ላይ ይገኛል። እንዲሁም የገበያ ጥናት ማኑዋል ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ከተዘጋጀው ማኑዋል በመነሳት ለገበያ ጥናት የስልጠና ዶክመንት ተዘጋጅቷል። ለስልጠና እና ለስራ ማስጀመሪያ የሚያስፈልገው በጀት የተዘጋጀ ሲሆን የገበያ ጥናት የሚሰራባቸው መድኃኒቶችም ተመርጠዋል፤ ስራውንም ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ሌሎች ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI5:** የተገላባጭ ፈንድ የገንዘብ መጠንን በ 10% መጨመር - አፈፃፀሙን ለመለካት ጥናት እየተካሄደ ነው።

**KPI6:** በወቅቱ ሥራ ላይ የዋለና የተወራረደ የጤና ፕሮግራሞች ፈንድ - አፈፃፀም 78.7%

**KPI7:** Cash to cash cycle time (in months) ወደ 12 ወር ማሳጠር- አፈፃፀሙን ለመለካት ጥናት እየተካሄደ ነው።

**KPI8:** የመድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች የብክነት መጠን ከ 2% በታች ማድረስ- አፈፃፀም 1% ነው።

**KPI9:** የውስጥ አሰራርን በማሻሻል የተቀነሰ ወጪ- አፈፃፀሙን ለመለካት ጥናት እየተካሄደ ነው።

**KPI10:** የፋይናንስ ሪፖርቶች ወቅታዊነት 100% ማድረስ (Financial reporting timelines) - አፈፃፀም 100% ነው።

## 3.4. የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦትን ማጎልበት

ስትራቴጂክ እርምጃዎች እና አፈጻጸማቸው

### 3.4.1. ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ማጠናከር

ለቅርንጫፎች የመድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ክምችት አያያዝና ስርዓት ሂደት የሚገልፅ የክምችት ትንተና (ABC & VEN analysis) ለማዘጋጀት ስልጠና ተሰጥቶ የትንተና ቅፅ የተሰራጨ ሲሆን አዲስ አበባ፣ መቀሌ፣ ሐዋሳ፣ አዳማ፣ ባህርዳር፣ ጅማ ቅርንጫፎች የክምችት ትንተና አዘጋጅተዋል። የተቀሩት ቅርንጫፎች ትንተናውን እንዲሰሩ ክትትል በመደረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም የኤጀንሲውን የግዥ መዘርዝር ከቅርንጫፎች ሁኔታ አንፃር በመነሳት VEN ክፍፍል ተዘጋጅቷል።
ህይወት አድን መድሃኒቶች በየወሩ በኤጀንሲዉ መጋዘኖች (በዋና መ/ቤትና ቅርንጫፎች) ያለ በግዥ እና ትራንዚት ሂደት ያለውን ክምችት ልየታ በማድረግ ከወቅታዊ ፍጆታ ጋር በማነፃፀር የክምችት ይዘት ሪፖርት ተሰርቷል። በዚህም መሰረት የህይወት አድንና የመሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት በመደበኛ ፕሮግራም 90.7% እንዲሁም በጤና ፕሮግራም 95% ነው።

በተገላባጭ ፈንድ ተገዝተው የሚቀርቡ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ትንበያና የአቅርቦት ዕቅድ ለማጠናከር የኤጀንሲውን ግዥ መዘርዝር መነሻ በማድረግ ትንበያ ተዘጋጅቶ ለ 2012 በጀት ዓመት ግዥ ትንበያ የተዘጋጀ ሲሆን

ትንበያውን የመተንተን ስራ ተሰርቷል። እንዲሁም የግዥ ጥያቄም የሃገር ውስጥ አምራቾችን የፍሬምዎርክ ግዥን በመለየት ተዘጋጅቷል።

የቲቢ፣ ወባ እና ለተመረጡ የኤች.አይ.ቪ መድኃኒቶች የግዥ ትንበያና ክለሳ የተሰራ ሲሆን የቤተሰብ ምጣኔ፣ የወባ፣ የኤች.አይ.ቪ ኤድስ በየሩብ ዓመቱ የአቅርቦት ዕቅድ ክትትል (Supply Plan Monitoring) ተሰርቷል። በመድኃኒት አስተዳደር ዙሪያ በቲቢ፣ ቴስት ኪት፣ ካንሰር፣ የክትባት አጠቃቀም (EVMA) ዙሪያ የዳሰሳ ጥናቶች ተካሂደዋል። የክትባት ግብዓቶች መጠየቂያ ፎርም (VRF) ታትሞ እንዲሰራጭ ተደርጓል። እንዲሁም በፍሬምዎርክ ለተጠየቁ የላቦራቶሪ ፕሌስመንት ማሽንና ሪኤጀንቶች የስርጭት እና የፍጆታ ክትትል በመደረግ ላይ ነው።

በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ፣ ቲቢ፣ ወባ እንዲሁም የቤተሰብ ምጣኔ ፕሮግራሞች ላይ በተመረጡ መድኃኒቶች ላይ የትንበያ ትክክለኛነት (Forecast Accuracy) የተሰራ ሲሆን ለጤና ፕሮግራም መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት በአማካይ 82.78% ሲሆን ለተመረጡ በተገላባጭ ፈንድ ተገዝተው የሚቀርቡ መድኃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የትንበያ ትክክለኛነት ደግሞ 62.3% ነው:: እንዲሁም አዲስ የሚመጡ የፀረ ኤች.አይ.ቪ መድኃኒቶችን በተመለከተ የስልጠና ማቴሪያል ተዘጋጅቶ ከክልሎች እና ከቅርንጫፎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ከዚህ በተጨማሪም Integrated Pharmaceuticals Logistics System የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የጥናቱ ሪፖርት ተጠናቆ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አውደ ጥናት የተካሄደ ሲሆን በአውደ ጥናቱ የተገኙ ሃሳቦችም እንዲካተቱ ተደርጓል።

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI11:** የመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ፍላጎት ትንበያ ትክክለኛነት አሁን ካለበት ከ 75% በላይ ማሳደግ፤አፈጻጸም- በጤና ፕሮግራም 82.78%፣ በመደበኛ ፕሮግራም 62.3% ነው።

**KPI12:** የህይወት አድንና የመሰረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦትን ከ 69% ወደ 95% ማድረስ፤ አፈጻጸም- በመደበኛ ፕሮግራም 90.7% እንዲሁም በጤና ፕሮግራም 95% ነው።

### **3.4.2.** የግዥ ጨረታ አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር

የግዥ ጨረታ አስተዳደር ስርዓቱን ለማጠናከር በተያዘው ዕቅድ መሰረት ለ 2011 የሚያስፈልጉ የፕሮግራምና የመደበኛ መድኃኒቶች፣ የህክምና መገልገያዎችና ኬሚካሎች ግዥ የተጠናቀቀ ሲሆን በዚሁ መሰረት ተገቢውን የጨረታ ዘዴ በመጠቀም በመደበኛ በጀት የብር 7,279,868,774.62 ዋጋ ያላቸው እንዲሁም በጤና ፕሮግራም የብር 5,947,562,179.78 ዋጋ ያላቸው በድምሩ የብር 13,227,430,954.40 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች የግዥ ትዕዛዝ ይዘዋል።

የሄማቶሎጂ፣ ኬሚስትሪ እና የስኳር መመርመሪያ ማሽኖች በፕሌስመንት የማዕቀፍ ግዥ (placemenet teneder) ተከናውኖ የሶስት ዓመት የረጅም ጊዜ የግዥ ፍሬምዎርክ ስምምነት ተፈጽሞ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ከፍተኛ የዋጋ ቅናሽ ተገኝቶበታል። እንዲሁም የህክምና መሳሪያዎች ድህረ ሽያጭ አገልግሎት ሰነድ ተዘጋጅቷል። የ 50 ማሽኖች ተከላ ተጠናቋል። ከዚህ በተጨማሪም 170 ለሚሆኑ የተለያዩ ጤና ተቋማት የህክምና መሳሪያ ተከላ፣

የማሽን ተከላ ዝግጅት፣ የማስጀመሪያ ሰነድ ዝግጅት እና የቦታ ልየታ ስራ እንዲሁም ወደ ኤጀንሲው መጋዘን የገቡ ለተለያዩ አይነት የህክምና መሳሪያዎች ኢንስፔክሽን ተሰርቷል።

በኤጀንሲው የሚከናወኑ ግዥዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲጠናቀቁ የቅድመ ግዥ አስተዳደር ስርዓትን በመከታተል የግዥ ጥያቄዎች በመጡበት ቅፅበት የጨረታውን ዘዴ በመወሰን የግዥ ፍቃድ እንዲጠየቅና የተጠየቀው የግዥ ፍቃድን በመከታተል እንዲሁም ለተፈቀዱ የግዥ ጥያቄዎች የጨረታ ሰነድ መዘጋጀቱንና ሌሎች አስፈላጊ ሂደቶች መሟላታቸውን በመከታተል የሚወስደውን ጊዜ መቀነስ ተችሏል። የድህረ ምዝና ሂደቱን በመከታተልና አስፈላጊውን የግንኙነት መረብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመፍጠር አስፈላጊ መረጃዎችን በተፈለገው የጊዜ ገደብ እንዲያመጡ ማድረግ ተችሏል።

የጨረታ ምዘና ጊዜን መቀነስ የሚያስችለው ዋነኛው መንገድ ግዥዎችን በማዕቀፍ ስምምነት መፈጸም ሲሆን ለሶስት ዓመት አገልግሎት የሚውል 26 የጸረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒቶች ግዥ ተከናውኗል። እንዲሁም ከ 2012 በጀት ዓመት ጀምሮ ለተከታታይ ሶስት ዓመታት አገልግሎት ላይ የሚዉሉ ከ 350 በላይ የሚሆኑ መድኃኒቶች፣ የህክምና መገልገያዎችና ኬሚካሎችን በማእቀፍ ግዥ ለመግዛት የአፈጻጸም መመሪያ በማዉጣት ጨረታ ወጥቶ ምዘናዉ ተጠናቋል።


የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI13:** የግዥ ጥያቄ ከቀረበበት የግዥ ትዕዛዝ እስከሚይዝበት ያለውን ቀን ወደ 90 ቀን ማድረስ- አፈፃፀም- በአማካይ 120.21 ቀናት (በቀጥታ ግዥ በአማካይ 92.43 ቀናት ሲሆን በግልፅ ጨረታ ደግሞ በአማካይ 148) ወስዷል።

**KPI14:** የግዥ ትዕዛዝ ከያዘበት እስከ ኮንትራት የሚፈረምበት ያለውን ቀን ወደ 15 ቀን ማሳጠር- አፈጻጸም በአማካይ 24.3 ቀናት ወስዷል።

**KPI15:** የግዥ ሂደት የሚወስደውን ቀን (Procurement Lead Time) አሁን ካለበት 280 ቀን ወደ 160 ቀን ማሳጠር- አፈፃፀም- 252 ቀናት ወስዷል።

የኤጀንሲው የግዥ ሂደት የወሰደው ጊዜ




### **3.4.3.** የሀገር ውስጥ አምራቾች አፈጻጸም

የሀገር ውስጥ አምራቾችን አቅም ለማጠናከርና በመንግስት የተያዘውን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ ለሃገር ውስጥ አምራቾች 25% የዋጋ ከለላ እየተደረገ ይገኛል። እንዲሁም የውሉን 30% ቅድመ ክፍያ እየተሰጠ ይገኛል። የሃገር ዉስጥ አምራቾችን ብቻ በመጋበዝና በዓለም አቀፍ ግልጽ ጨረታዎች ላይ በመሳተፍ ከአጠቃላይ የግዥ ትዕዛዝ ዉስጥ ብር 1,594,814,935.80 የሚሆነዉ ለሃገር ዉስጥ አምራቾች የተሰጠ ነዉ። የሃገር ውስጥ አምራቾች በበጀት ዓመቱ ውስጥ ማቅረብ ከሚጠበቅባቸው የብር 1,781,816,053.96 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ውስጥ የብር 1,065,740,453.14 (59.8 %) ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎችን አቅርበዋል።

## የ 2011 በጀት ዓመት የሃገር ውስጥ አምራቾች አቅርቦት አፈፃፀም

| ተ.ቁ | አቅራቢ | የግዥ ትእዛዝ ቁጥር | የመድሃኒት አይነት ብዛት | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የመድሃኒት አይነት ዉስጥ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት (%) ከእያንዳንዱ የግዥ ትእዛዝ አንጻር | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የግዥ ትእዛዝ ዉስጥ በአማካይ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አዲስ መድሃኒት ፋብሪካ | 4633 | 23 | 42 | 42.8% |
| | | 4547 | 6 | 27.3 | |
| | | 4707 | 2 | 59 | |
| | | 4768 | 3 | 5 | |
| | | 4861 | 1 | 3 | |
| | | 4747 | 1 | 39 | |
| | | 4831 | 1 | 96 | |
| | | 4907 | 1 | 75 | |
| | | 4962 | 18 | 25 | |
| | | 5059 | 1 | 100 | |
| | | 4952 | 1 | 0 | |
| 2 | ካዲላ መድሃኒት ፋብሪካ | 4630 | 10 | 64 | 48.6% |
| | | 4553 | 3 | 86 | |
| | | 4623 | 1 | 0 | |
| | | 4955 | 1 | 100 | |
| | | 4974 | 7 | 60 | |
| | | 5012 | 1 | 30.7 | |
| | | 4715 | 1 | 0 | |
| 3 | ኢስት አፍሪካ መድሃኒት ፋብሪካ | 4631 | 4 | 68 | 54.5% |
| | | 4971 | 4 | 41 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ኢትዮጵያ መድሃኒት ፋብሪካ | 4634 | 26 | 59 | 48.6% |
| | | 4556 | 11 | 45 | |
| | | 3940 | 1 | 41 | |
| | | 3941 | 1 | 37 | |
| | | 4451 | 1 | 43.5 | |
| | | 4356 | 1 | 100.1 | |
| | | 4843 | 1 | 67 | |
| | | 4970 | 6 | 45 | |
| | | 4839 | 1 | 0 | |
| ተ.ቁ | አቅራቢ | የግዥ ትእዛዝ ቁጥር | የመድሃኒት አይነት ብዛት | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የመድሃኒት አይነት ዉስጥ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት **(%)** ከእያንዳንዱ የግዥ ትእዛዝ አንጻር | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የግዥ ትእዛዝ ዉስጥ በአማካይ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት |
| 5 | ፈውስ መድሃኒት ፋብሪካ | 4632 | 1 | 100 | 100% |
| 6 | ሂዩማን ዌል መድሃኒት ፋብሪካ | 4561 | 9 | 68 | 48.5% |
| | | 4635 | 2 | 50 | |
| | | 4687 | 1 | 95 | |
| | | 4636 | 2 | 0 | |
| | | 4713 | 7 | 22 | |
| | | 4627 | 4 | 41 | |
| 7 | ጁልፋር መድሃኒት ፋብሪካ | 4018 | 1 | 100 | 80.9% |
| | | 4090 | 1 | 100 | |
| | | 4091 | 1 | 100 | |
| | | 4092 | 1 | 100 | |
| | | 4628 | 5 | 64.5 | |
| | | 4564 | 4 | 67.7 | |
| | | 4969 | 4 | 34 | |
| 8 | ሜድሶል መድሃኒት ፋብሪካ | 4968 | 1 | 100 | 50% |
| | | 5043 | 1 | 0 | |
| 9 | ፋርማኪዩር መድሃኒት ፋብሪካ | 4973 | 1 | 57 | 45% |
| | | 4954 | 1 | 33 | |
| 10 | ሳንሼንግ መድሃኒት ፋብሪካ | 4583 | 5 | 20 | 31% |
| | | 4714 | 1 | 0 | |
| | | 4771 | 2 | 0 | |
| | | 4972 | 4 | 42 | |
| | | 4987 | 1 | 0 | |
| | | 4629 | 15 | 39 | |
| | | 5042 | 2 | 20 | |
| | | 5034 | 1 | 0 | |

| ተ.ቁ | አቅራቢ | የግዥ ትእዛዝ ቁጥር | የመድሃኒት አይነት ብዛት | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የመድሃኒት አይነት ዉስጥ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት (%) ከእያንዳንዱ የግዥ ትእዛዝ አንጻር | እንዲያቀርቡ ከተሰጣቸዉ የግዥ ትእዛዝ ዉስጥ በአማካይ ገቢ ያደረጉት መጠን በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | አክሰስ ባዮ እንተርናሽናል | 4885 | 1 | 95.92 | 95.92% |
| 12 | አዳሚ ቱሉ ፀረ-ተባይ ማምረቻ | 4464 | 1 | 65 | 65% |
| 13 | አምቫጅ ማምረቻ ኃ/የ/ግ/ማ | 3348 | 2 | 53.2 | 53.2% |
| 14 | አስሚ እንዱተሪያል | 3630 | 4 | 8.5 | 4.25% |
| | | 3349 | 5 | 0 | |
| 15 | ዳሉል ፋርማሱቲካል | 4266 | 4 | 25 | 39% |
| | | 3347 | 3 | 53 | |
| 16 | ዳና ትሬድንግ | 4661 | 1 | 100 | 100% |
| 17 | ፋክት ሄልዚ | 3342 | 1 | 100 | 100% |
| 18 | ፋኑስ ሜተክ | 4662 | 1 | 0 | 23.6% |
| | | 4446 | 1 | 75.2 | |
| | | 4447 | 1 | 7.4 | |
| | | 4448 | 1 | 13.1 | |
| 19 | ፋይን ኬምካልስ | 3346 | 1 | 40.7 | 40.7% |
| 20 | ፎሊም ትሬዲንግ ኃ/የ/ግ/ማ | 4267 | 2 | 59 | 33% |
| | | 3344 | 1 | 7 | |
| 21 | ሙብ ትሬዲንግ ኃ/የ/ግ/ማ | 4708 | 1 | 95 | 95% |
| 22 | ኪዊንስ ሀይጂኒክ እንዱስትሪ | 3343 | 1 | 96.2 | 96.2% |
| 23 | ሳሚድ ኃ/የ/ግ/ማ | 4637 | 2 | 50 | 50% |
| 24 | ሼባ ፋርማሱቲካል | 3345 | 2 | 100 | 100% |
| | | 4584 | 1 | 100 | |
| 25 | ሸግና ፋርማሱቲካል | 4248 | 1 | 100 | 100% |
| 26 | ተኪያ ዘራይ ፕላስቲክ ፋብሪካ | 4912 | 1 | 100 | 100% |
| 27 | ዋሴ ፋርማሱቲካል | 3350 | 2 | 89 | 89% |
| 28 | ሲ.ጂ.ኤፍ ቢዝነስ ግሩፕ | 4338 | | 4.94 | 43% |
| | | 4339 | | 81 | |
| 29 | አብርሀም ገ/ኢግዝሀበር ፋሻማምረቻ | 3691 | | 17 | 8.5% |
| | | 3692 | | 0 | |

### 3.4.4. የኮንትራት አስተዳደር ስርዓቱን ማጠናከር

በበጀት ዓመቱ ወደ መጋዘን የገቡ መድኃኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

| ተ.ቁ. | ዝርዝር ተግባራት | ምድብ **(category)** | ወደ መጋዘን የገቡ ጠቅላላ ዋጋ በብር |
|---|---|---|---|
| 1 | በመደበኛ በጀት ከውጭ ሃገር ተገዝተዉ ወደ መጋዘን የገቡ | መድኃኒቶች | 1,241,157,804.34 |
| | | የህክምና መሳሪያ | 450,231,188.01 |
| | | የህክምና መገልገያ | 325,056,461.59 |
| | | ኬሚካል እና ሪኤጀንት | 236,716,395.57 |
| ድምር ከውጭ ሃገር | | | **2,253,161,849.51** |
| 2 | መደበኛ በጀት ከሃገር ውስጥ ተገዝተዉ ወደ መጋዘን የገቡ | መድኃኒቶች | 661,044,578.08 |
| | | የህክምና መገልገያ | 72,388,018.10 |
| | | ኬሚካል እና ሪኤጀንት | 239,666,289.56 |
| ድምር ከሃገር ውስጥ **(RDF)** | | | **973,098,885.74** |
| በመደበኛ በጀት ተገዝተው ወደ መጋዘን የገቡ አጠቃላይ ድምር | | | **3,226,260,735.25** |
| 3 | በጤና ፕሮግራም (GF & SDG) ከውጭ ሃገር ተገዝተዉ ወደ መጋዘን የገቡ | መድኃኒቶች | 1,027,739,296.91 |
| | | የህክምናመሳሪያ | 208,823,981.16 |
| | | የህክምናመገልገያ | 120,616,620.29 |
| | | ኬሚካልእናሪኤጀንት | 191,617,278.22 |
| አጠቃላይ ድምር (**GF & SDG**) | | | **1,548,797,176.58** |
| 4 | ከአጋር ድርጅቶች በዓይነት (In kind) ወደ ኤጀንሲው መጋዘን ገቢ የሆኑ **(MOH, UNICEF & Others)** | መድኃኒቶች | 9,571,583,365.84 |
| | | የህክምናመሳሪያ | 16,121,301.59 |
| | | የህክምናመገልገያ | 81,083,270.84 |
| | | ኬሚካልእናሪኤጀንት | 40,396,652.17 |
| ጠቅላላ ድምር **(MOH, UNICEF & Other)** | | | **9,709,184,590.44** |
| በበጀት ዓመቱ በአጠቃላይ በመደበኛ በጀት እና በጤና ፕሮግራም ወደ ኤጀንሲው መጋዘን የገቡ | | | **14,484,242,502.27** |

በበጀት ዓመቱ ከብሔራዊ ባንክ ከGF & SDG የባንክ አካውንት 140,155,304.00 ዶላር ተፈቅዶ 127,420,837.94 ዶላር ዋጋ ያላቸው የግዥ ትዕዛዞች LC/CAD በወቅቱ እንዲከፈት ተደርጓል።

በመደበኛ በጀት ከኤጀንሲው የውጭ ምንዛሬ አካውንት 9,812,000.34 ዶላር ከብሔራዊ ባንክ ተጠይቆ ከአንድ የግዥ ትእዛዝ ውጭ ያሉት የግዥ ትዕዛዞች LC/CAD የተከፈተላቸው ሲሆን መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች እየገቡ ይገኛሉ። በበጀት ዓመቱ ውስጥ 83,000,000 ዶላር ከብሔራዊ ባንክ ተፈቅዷል። በአጠቃላይ ለመደበኛ የ 92,812,000.34 ዶላር ፍቃድ ተገኝቷል።

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI16:** ለመድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዥ LC/CAD ከተከፈተበት ጊዜ አንስቶ ወደብ ላይ እስከደረሰበት ያለውን ጊዜ ወደ 90 ቀናት ማድረስ (Supplier lead time variability) አፈጻጸም- በአማካይ 78.5 ቀናት ወስዷል።

**KPI17:** መድሃኒትና ህክምና መሳሪያዎች ግዥ ወደብ ላይ ከደረሰበት ቀን አንስቶ ወደ ኤጀንሲው መጋዘኖች ገቢ የተደረገበትን ከ25 ቀናት በታች ማድረስ- አፈጻጸም- በአማካይ 29 ቀናት ወስዷል። (በባህር ተጭነው የሚመጡትን በአማካይ በ48 ቀናት እንዲሁም በአየር ተጭነው የሚመጡትን በአማካይ በ10 ቀናት ወደ መጋዘን እንዲገቡ ተደርጓል።)

**KPI18:** አቅራቢዎች በውሉ መሰረት ማቅረብ የሚገባቸውን ያቀረቡበት መጠን /Supplier fill rate/- አፈጻጸም አልተለካም

### 3.4.5. የመጋዘን አያያዝና የክምችት አስተዳደር ሥርዓት ማጠናከር

በተመረጡ 8 ቅርንጫፎች ላይ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ማስወገጃ ኢንሲኔሬተር ግንባታና ተከላ ለማከናወን በተያዘው ዕቅድ መሰረት ስምንቱ ኢንሲኔሬተሮች ሃገር ውስጥ ገብተው በየቅርንጫፎቹ የደረሱ ሲሆን በ6 ቅርንጫፎች የግንባታ ስራው 80% ተጠናቋል። እንዲሁም በአዳማ፣ በሃዋሳ እና በባህርዳር ቅርንጫፎች ላይ የግንባታ ስራው እና የኢንሲኔሬተር ተከላው ተጠናቋል። ከዚህ በተጨማሪም በመቀሌ፣ በነቀምት እና በደሴ ቅርንጫፎች የኢንሲኔሬተር ተከላው ተጠናቋል። የጅማ እና የጅግጅጋ ቅርንጫፎች ግንባታ ተጀምሯል።

የGPS ተከላ እና ስልጠና ተጠናቋል፤ የአፈፃፀም መመሪያ ፀድቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል። የዋናው መስሪያቤት እና የ17 መጋዘኖች CCTV፣ Door Intrusion፣ Smoke Detection and Protection ተከላ የሲቪል ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ማስተካከያ ተደርጓል። እንዲሁም በሁሉም ቅርንጫፎች የደህንነት ካሜራዎችን እና ሌሎችን የሚያስተዳድሩ ባለሙያዎች እንዲቀጠሩ ተደርጓል።

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የክምችትና ስርጭት አስተዳደርን አፈጻጸም ለማሻሻል ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ ተብሎ ከተለየውና ትኩረት ከሚያስፈልጋቸው አንዱ የቆጠራ ትክክለኛነትን ማሻሻል ነው። ይህም በቆጠራ የሚገኝ ውጤት ቢን ካርድ ላይ ከሚጻፈው ጋር ተመሳሳይ መሆን ይኖርበታል። በዚህም መሰረት በዋናው መስሪያ ቤት መጋዘኖች በተካሄደ ዳሰሳ የክምችት ቆጠራ ትክክለኛነት 86.8% ነው።

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የክምችት ትክክለኛነትን ለመጨመር በዋናው መስሪያ ቤት በየቀኑ ቆጠራ እየተካሄደ ሲሆን በሚገኘው ውጤት መሰረትም የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል። የመጋዘን አያያዝን ለማሻሻል በየሳምንቱ የGDP (Good Distribution Practice, Warehouse, yard cleanless and cold room) ምዘና እየተሰራ ሲሆን ብዙ መሻሻልም ታይቷል።

በበጀት ዓመቱ በኤጀንሲው መጋዘኖች ውስጥ የመደበኛ በጀት የብር 3,186,829,500.45 እና የብር 9,380,823,056.98 ዋጋ ያላቸው የጤና ፕሮግራም መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች በክምችት

ይገኛል፤ ከዚህ ውስጥ የብር 4,223,058,882.09 ዋጋ ያላቸው Azithromycine, Ivermectin, Radiotherapy-Linear Accelerator - Clinac iX, Lamivudine + Nevirapine + Zidovudine - (150mg + 200mg + 300mg) - Tablet, Lamivudine + Efavirenz +Tenofovir - (300mg + 400mg + 300mg)- Tablet, X Ray - Radiography with Fluoroscope – Digital - FDR Smart FGX-68S, Chemical-Potassium Iodate - Powder, Water Treatment and Purification-67mg - Tablet, Pentavalent (DTP-Hib-Hep) Vaccine - Injection, HIV Rapid Test-First Test Kit, Stat-Pack መድኃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች በክምችት የሚገኙ ናቸው። በኤጀንሲው መጋዘኖች ካለው ክምችት ውስጥ በመደበኛ በጀት የብር 141,794,469.43 እንዲሁም በጤና ፕሮግራም የብር 126,868,882.39 በድምሩ የብር 268,663,351.82 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ስድስት ወርና ከዛ በታች የመጠቀሚያ ጊዜ ያላቸው ናቸው።

የክትባት መድሃኒት አያያዝ ሽግግር በሁሉም ቅርንጫፎች ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ወደ ወረዳ የቀጥታ ስርጭት 96% ሆኗል። የአሰራር ጥራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ለመስራት የታቀደ ሲሆን በሁሉም ቅርንጫፎች ያለውን የክትባት አያያዝና አስተዳደር ስርዓት የሚያሳይ የ EVM ዳሰሳ ጥናት ተሰርቶ ክፍተቶችን በመለየት የማሻሻያ ዕቅድ ተዘጋጅቶ የጋራ የምክክርና የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

የአፈጻጸም መለኪያዎች


- **KPI19:** የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች መጠየቂያና ሪፖርት ማድረጊያ የላኩ **(**RRF reporting rate)- ወደ 95% ማድረስ፡- አፈጻጸም ለጤና ፕሮግራም 83.3%፣ ለመደበኛ በጀት 96% ነው።
- **KPI21:** የክምችት ቆጠራ ትክክለኛነት (Inventroy accuracy rate) 100% ማድረስ- አፈጻጸም 86.8% ነው።
- **KPI22**፡ የክምችት መገላበጥ በአማካይ በዓመት አሁን ካለበት ወደ 1.8 ማድረስ- አፈፃፀሙን ለመለካት ጥናት እየተካሄደ ነው።
- **KPI23**፡ የጭነት ትዕዛዝ መጋዘን ደርሶ እስኪጫን ያለው አማካይ ጊዜ (Order around time or warehouse order cycle time) ወደ 2 ሰዓት ማድረስ- አፈጻጸም 3 ሰዓት ነው።
- **KPI24**፡ በዝቅተኛና ከፍተኛ መጠን መካከል የተከማቹ መድሃኒቶችና ህክምና መገልገያዎች (Percentage of stock status observations in storage sites where pharmaceuticals stocked according to plan) ለመድሃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች መጋዘን ከገባበት አንስቶ ወደ ፋይናንስ ለማስተላለፍ የሚወስደውን ጊዜ 3 ቀን ማድረስ- አፈጻጸም- ከሃገር ውስጥ ገቢ ለሚደረጉ መድሃኒቶች በ 1.5 ቀን፣ ከውጪ ተገዝተው ለሚገቡ መድሃኒቶች 6.5 ቀን ነው።

**3.4.6.**የስርጭት እና ተሽከርካሪዎች ስምሪት አስተዳደር ስርዓት ማጠናከር

ኤጀንሲው ለመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ስርጭት የሚጠቀምባቸውን ተሽከርካሪዎች አጠቃቀም ዘመናዊ ለማድረግና ለማሻሻል የሚያስችል የጂፒኤስ ተከላ በሁሉም ተሽከርካሪዎች ላይ ተጠናቆ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች ስርጭት የሚወስደውን ጊዜ ለማሳጠር በታቀደው መሰረት ቅርንጫፎች ከማዕከል መጋዘኖች መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያዎች እንዲቀርቡላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካኝ ጊዜ 8 ቀናት ወስዷል።

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የብር 3,283,136,406.26 ዋጋ ያላቸው የመደበኛ በጀት እና የብር 13,736,689,413.00 ዋጋ ያላቸው የጤና ፕሮግራም በድምሩ የብር 17,019,825,819.26 ዋጋ ያላቸው መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ስርጭት ተከናውኗል። መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች የጤና ተቋማትን ፍላጎት በዓይነትና በመጠን በመለየት ለ 421 ሆስፒታሎች፣ ለ 2,401 ጤና ጣቢያዎች፣ ለ 867 ወረዳ ጤና ፅህፈት ቤቶችና ለ 81 የዞን ጤና መምሪያዎች በየሁለት ወሩ በተቀናጀ መልክ በቀጥታ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።




የ **2010** እና የ **2011** በጀት ዓመት የመደበኛ በጀትና የጤና ፕሮግራም ስርጭት

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI125:** ጤና ተቋማት ከቅርንጫፎች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካኝ ጊዜ ወደ 1 ቀን መቀነስ- አፈፃፀም- አልተለካም

**KPI26**፡ ቅርንጫፎች ከማዕከል መጋዘኖች መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብላቸው ከጠየቁበት እስከ ተሰራጨበት ያለው አማካይ ጊዜ ከ 13 ቀናት ወደ 8 ቀናት መቀነስ-አፈፃፀም 8 ቀናት ነው።

**KPI27:** ጤና ተቋማት ድንገተኛ መድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች እንዲቀርብ ከጠየቁበት አገልግሎቱን ያገኙበት አማካይ ጊዜ (Average time from request to product dispatch) ወደ ግማሽ ቀን መቀነስ- አልተለካም

**KPI28:** የተሰበሰበ የመድሃኒትና ህክምና መገልገያዎች የስርጭት ርክክብ ማረጋገጫ ሰነድ (percentage of proof of delivery collected)-አፈጻጸም 91% ነው።

## 3.5. ተቋማዊ አቅምን ማጎልበት

ስትራቴጂክ እርምጃዎች እና አፈጻጸማቸው

### 3.5.1. የሰው ሃብት ልማትና አስተዳደር ማጎልበት

የኤጀንሲው የሰው ሃይል ልማትን ለማጎልበት የሚያስችል የሶስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል። እንዲሁም ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን የአተገባበር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል። የኤጀንሲውን የሰራተኞች ፍልሰት (Turn Over) ለመቀነስ እንዲሁም ብዙ ያገለገሉና ጥሩ ልምድ ያላቸውን ሰራተኞች ለማቆየት እንዲቻል የሰራተኞች የማትጊያ ስርዓት ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቷል። እንዲሁም በየስራ ሂደቱ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎችን መሠረት ያደረገ የእዉቀትና የክህሎት መስፈርቶችን የማዘጋጀት ስራ ተጀምሯል። ይህንን መሰረት በማድረግ በየስራ ሂደቱ ፈፃሚ ባለሙያዎች ከተለዩት መስፈርቶች (Competency Requirements) አንፃር ያሉባቸዉ ክፍተቶች በመለየት (Competency Mapping) በመስራት አስፈላጊ ስልጠናዎችና ሌሎች የአቅም ግንባታ ስራዎች ለማከናወን ከ PSA ጋር በመተባበር Competency Framework እየተሰራ ይገኛል። ለኤጀንሲው 18 ሰራተኞች የትምህርት ዕድል በማመቻቸት በመደበኛ ፕሮግራም የድህረ ምረቃ ትምህርት በመማር ላይ ይገኛሉ።

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI29:** የሰው ኃይል ፍልሰት ከ 3.72% ወደ 3% መቀነስ- አፈጻጸም 4.76% ሆኗል።

### 3.5.2. የአቅርቦት ሰንሰለት መሠረተ ልማት ማጎልበት

የኤጀንሲዉ ዋና መስሪያ ቤት የ 2B+G+7 የቢሮና የቀዝቃዛ ሰንሰለት የማጠናቀቅ (Finishing) ግንባታ ስራ ግዥውን ለማከናወን ለሁለተኛ ግዜ በአለም አቀፍ የግዥ ዘዴ ጨረታ አየር ላይ ውሎ የቴክኒክ ግምገማ ተጠናቆ የቴክኒክ ውጤት ለተጫራቾች እንዲገለፅ የተደረገ ሲሆን በቴክኒክ ግምገማ ላይ የቀረበው ቅሬታ በመስሪያቤቱ መልስ የተሠጠ ቢሆንም በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ቅሬታው በመቅረቡ በኤጀንሲው ቦርድ እየታየ ይገኛል።

የቢሮ እጥረት ችግርን ለመቅረፍ ነባሩን መጋዘን ለቢሮ ምቹ በሆነ መልኩ በመገንባት አገልግሎት ላይ ለማዋል በተገባው የውል ስምምነት መሰረት የግንባታ ስራው ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

የኤጀንሲው ንብረት የሆነ 1 አይሱዙ እና 3 ፒክአፕ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ለረዥም ጊዜ ቆመው የነበረ ሲሆን በውስጥ አቅምና በካምፓኒ መሰራት የማይችሉትን በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ በማወዳደር ከአሸናፊው ጋር ውል ተፈጽሞ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው ወደ ስራ ገብተዋል። ከዚህ በተጨማሪም 6 የተለያየ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎች በሌላ ውጭ ጋራዥ ተጠግነው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል። እንዲሁም በኤጀንሲው ያለውን የተሽከርካሪ እጥረት ችግር ለመቅረፍ የተለያየ መጠን ያላቸው 15 አውቶ ሞቢል እና 2 ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎችን በግልፅ ጨረታ ግዥ ለመፈፀም ውል የተገባ ሲሆን ሁለቱ ፒክ አፕ ተሽከርካሪዎች ገቢ ሆነው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል።

የአፈጻጸም መለኪያዎች

**KPI31**፡ የመጋዘን ቦታ አጠቃቀም ከ 67% ወደ 85% ማሳደግ- አፈጻጸም- 62% ሆኗል።

**KPI32**፡ የጭነት መኪኖች አቅርቦት ወደ 100% ማሳደግ-አፈፃፀሙም 72% ነው።

**KPI33**፡ የጭነት ተሽከርካሪዎች የስርጭት አገልግሎት የማይሰጡበት ጊዜ መጠን (Vehicle down time) ወደ 14% መቀነስ-አፈፃፀሙም 23% ነው።

### 3.5.3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ፈጠራን ማጎልበት

ኤጀንሲው የሚጠቀምበት የጤና ግብዓት መረጃ ስርዓት HCMIS ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመከታተል እንዲፈቱ ተደርጓል። እንዲሁም ተጨማሪ ፊቸሮች እንዲካተቱ አስፈላጊው ክትትል እየተደረገ ነው። የኤጀንሲው ድህረ-ገጽ በአዲስ መልኩ ተሰርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። www.epsa.gov.et እንዲሁም E-IPLS ን ተግባራዊ ለማድረግ ከተለያዩ የጤና ተቋማት የተዉጣጡ 78 የሚሆኑ ባለሙያዎች የሙከራ ትግበራ ያደረጉ ሲሆን በሙከራ ጊዜ ከተሳተፉ ባለሙያዎች የተሰጠውን ግብረመልስ በማካተት ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገባ ተደርጓል።

የተቀናጀ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት (ERP) ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በኤጀንሲው ያለውን የስራ ፍሰት በማጥናት የተቀላጠፈ አሰራር መቀየስ አስፈላጊ በመሆኑ (Business Process Transformation) የሥራ ፍሰት ማሻሻያ ጥናት ተደርጓል። እንዲሁም የሥራ ፍሰቱን የመፈተሽ እና በተሻሻለው የሥራ ፍሰት መሠረት የፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት ታቀዶ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን የሥራ ፍሰቱን ለመፈተሽ እንዲረዳ ከሁለት ቅርንጫፎች እና ከዋናው መስሪያቤት ከስድስት ዳይሬክቶሬቶች የተውጣጡ በአጠቃላይ 25 ባለሙያዎች በመመደብ እንዲሁም አማካሪ በመቅጠር ለሶስት ወራት የሥራ ፍሰት ማሻሻያ ጥናት ተከናውኗል። የኤጀንሲው የመረጃ አስተዳደር መመሪያ ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል።

### 3.5.4. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጎልበት

የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ለማጠናከር የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ትግበራው የተጀመረ ሲሆን ቁልፍ የአፈጻጸም መለኪያዎችን በኤጀንሲ ደረጃ (Corporate level KPIs)፣ በስራ ሂደት ደረጃ (Process level KPIs) እና ለእያንዳንዱ ፈጻሚ (individual level KPIs) ተዘጋጅቶ የአፈጻጸም መነሻ (baseline) መሰብሰቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለሁሉም ቅርንጫፎች ተልኳል። እንዲሁም በአራት ቅርንጫፎች ማለትም ሐዋሳ፣ አዳማ፣ ጅማ እና ደሴ ቅርንጫፎች ላይ የአፈጻጸም መነሻ ዳሰሳ ተካሂዷል። በክትትልና ግምገማ ማዕቀፉ ያሉ መለኪያዎች የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾች (tracking tools) ወጥ (standardize) እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን የአፈጻጸም መለኪያዎች ማብራሪያዎችን (Performance indicator reference sheet) የማጥራት ስራ ተሰርቷል።

በአዳማና በደሴ ቅርንጫፎች የክትትልና ግምገማ ትግበራ ሜንተርሽፕ የተሰጠ ሲሆን የቅርንጫፍ ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎች ወጥ እንዲሆኑ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪም የጤና ተቋማት (የደንበኞች) እና የሰራተኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት የጤና ተቋማትና የሰራተኞች እርካታ ዳሰሳ ለመስራት የሚያስችሉ ቱሎች ተዘጋጅተው በአዳማ ቅርንጫፍ የሙከራ ዳሰሳ የተካሄደ ሲሆን በሙከራ ዳሰሳው ውጤት መሰረትም ቱሎችን ሊያሰሩ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጓል። እንዲሁም ከቅርንጫፎች እና ከዋናው መስሪያቤት ለተውጣጡ 93 ስራ አስኪያጆች እና አስተባባሪዎች ጥናቱን ለማካሄድ የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት ስልጠና ማለትም በመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና ትንተና ዙሪያ በሶፍትዌር (Statistical Package for Social Science) በመጠቀም ሰልጣኞች መረጃ ለመተንተንና የዳሰሳ ጥናት ውጤቱን ሪፖርት ለማቅረብ የሚያስችላቸውን በተግባር የታገዘ በሁለት ዙር ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል። በዚህም መሰረት የጤና ተቋማት እና የሰራተኞች የእርካታ ዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ተደርጓል።

ለኤጀንሲው ቅርንጫፎች ድጋፋዊ ጉብኝት ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የድጋፋዊ ጉብኝት ቡድን ተቋቁሞ ቼክሊስትና ቢጋር በማዘጋጀት የተቀናጀ ድጋፋዊ ጉብኝት ሰሜንና ሰሜን ምዕራብ ክላስተር በሚገኙ ስድስት ቅርንጫፎች እንዲሁም በአራት ቅርንጫፎች የተቀናጀ ድጋፋዊ ጉብኝት የተደረገ ሲሆን የድጋፋዊ ጉብኝቱ ሪፖርት ተዘጋጅቷል።

የኤጀንሲውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚረዱ የአሰራር ሂደቶችን ለመቅረጽ የሚያስችሉ 6 የጥናት መስኮች የተለዩ ሲሆን መስፈርቶችን በማዘጋጀት የኤጀንሲዉ ሰራተኞች ሊያከናዉኗቸዉ በሚችሉዋቸዉ የጥናት መስኮች ላይ በቡድን በቡድን እንዲወዳደሩ በማድረግ በዉድድሩ አሸናፊ የሆኑ 5 ጥናት የሚያካሄዱ ቡድኖችን በመለየት ፕሮፓዛሎችን አዘጋጅተው ወደ ጥናት እንዲገቡ ተደርጓል።

የኤጀንሲውን አሰራር ጥራት ለማስጠበቅ የጥራት አስተዳዳር ስርዓት (Quality Management System) በዋናው መስሪያቤትና በሁሉም ቅርንጫፎች እንዲተገበር ስልጠና እንዲወስዱ የተደረገ ሲሆን የጥራት አስተዳደር ስርዓት ማንዋል ተዘጋጅቷል። እንዲሁም የጥራት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ፀድቋል።

### 3.5.5. የመድሃኒት አቅርቦት ለማረጋገጥ ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር

#### 3.5.5.1. የመልካም አስተዳደር እና ስነምግባር አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር

የኤጀንሲው መልካም አስተዳደር ዕቅድ የሴክተሩን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ተዘጋጅቷል። ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ዳይሬክቶሬቶችና ቅርንጫፎች እንዲያዘጋጁ ተደርጓል። በዚህም መሰረት በበጀት ዓመቱ ከተለዩት ዋና ዋና 30 የውስጥና የውጭ የመልካም አስተዳደር ችግሮች መካከል 23 ያህሉ ማለትም ከመጋዝን ወለል፣ ከመሰረታዊ የለውጥ ስራ ሂደት ምደባ፣ የአስተዳደር እርከኖች ግንኙነት፣ የስልጠና ኢፍትሃዊነት፣ የስራ ስምሪት፣ ከብክነት እና ከቸልኝነት ጋር ተያይዞ በተለያዩ መድረኮችና ውይይቶች የቀረቡ የመልካም አስተዳደር ችግሮች የተፈቱ ሲሆን 7 የመልካም አስተዳደር ችግሮች ማለትም የመድኃኒት ስርቆት፣ የመጋዝን ዘረፋና ከቅጥር ዝውውር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በውስጥ አሰራርና በህግ የተያዙ በመሆኑ በሂደት ላይ ይገኛሉ።

የኤጀንሲው የዜጎች ቻርተር (የአልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ) ተዘጋጅቶ የዋናው መስሪያ ቤት የዜጎች ቻርተር ተዘጋጅቶ 300 ኮፒ ታትሟል። ሁሉም የስራ ክፍሎችና ቅርንጫፎች የዜጎች ቻርተር (የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ) አዘጋጅተዋል። እንዲሁም የዜጎች ቻርተር በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት መስጠቱን ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በዘጠኝ የስራ ክፍሎች የዳሰሳ ጥናት በማከናውን በጥናቱ መሰረት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል። የቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓት ከማጠናከር አንጻር በመዝገብ ቅሬታ እንዲሰበሰብና ትንተና እንዲካሄድ ለማድረግ በታቀደው መሰረት 14 የውጭ ቅሬታዎች ቀርበው 10 ቅሬታዎች የተፈቱ ሲሆን 4 ቅሬታዎች በሂደት ላይ ይገኛሉ።

የሥነምግባር ጥምረት ከቅርንጫፎች 22 ሰራተኞች እና ከዋናው መስሪያቤት 12 አባላት በድምሩ 34 አባላት ያሉት የሥነምግባር ጥምረት ተቋቁሟል። እንዲሁም የሃብትና ንብረት ብክነት ሊኖርባቸው የሚችሉ 4 የስራ ሂደቶች ማለትም የሰው ሃብት አስተዳደርና ልማት፣ የመጋዘን አያያዝና የክምችት አስተዳደር፣ የኮንትራት አስተዳደር እና የጠቅላላ አገልግሎትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬቶች ተለይተዋል። የሙስና መከላከል ስትራቴጅክ ሰነድ ክለሳ የተጀመረ ሲሆን 5 የበላይ ኃላፊዎች የሃብት ምዝገባ እና ሌሎች የሚመለከታቸው 47 ሰራተኞች ሃብት የማስመዝገብ ስራ ተከናውኗል። እንዲሁም በመድሃኒት ስርቆት ላይ ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞችን የመለየት ስራ እየተከናወነ ይገኛል። በዋናው መስሪያቤት ለሚገኙ 456 ሰራተኞች በሥነ-ምግባርና በሙስና መከላከል ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል።

የካይዘን ፍልስፍና የሙከራ ትግበራ ለማስጀመር በተያዘው ዕቅድ መሰረት የካይዘን ፍልስፍና የሙከራ ትግበራ በተመረጡ ቅርንጫፎች ለማስጀመር በተያዘው ዕቅድ መሰረት በሃዋሳ፣ በመቀሌ፣ በባህርዳር እና በጅማ ቅርንጫፎች ለሚገኙ 508 ሰራተኞች ስልጠና በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ ተጀምሯል። በዚህም መሰረት የካይዘን ፍልስፍና ትግበራ ሂደት ወቅት በሃዋሳ ቅርንጫፍ በገንዘብ 560,404.00 ብር (አምስት መቶ ስልሳ ሺ አራት መቶ አራት ብር) ውጤት ማግኘት ተችሏል።

### **3.5.5.2.** የህግ አገልግሎት ስርዓት ማጠናከር

ኤጀንሲው ለተከሰሰባቸው የህግ ጉዳዮች መልስ በማቅረብ እና ለኤጀንሲው የተወሰነው እንዲፈጸም ክትትል ተደርጓል። በአጠቃላይ በፍርድ ቤት የሚገኙ 6 የፍትሃብሔር ጉዳዮች፣ በወንጀል ጉዳይ በፖሊስና በዓቃቢ ህግ የሚገኙ 9 ጉዳዮች እና በስራ ክርክር በፍርድ ቤት የሚገኙ 1 ጉዳዮች ናቸው። በፍትሃብሄር ጉዳይ ውሳኔ ያገኙ 9፣ በስራ ክርክር ውሳኔ ያገኙ 4፣ በወንጀል ጉዳይ ውሳኔ ያገኙ 1 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለኤጀንሲው የተወሰኑ የፍትሃብሄር ጉዳዮች 5፣ በኤጀንሲው ላይ የተወሰኑ የፍትሃብሄር ጉዳዮች 4 እና በኤጀንሲው ላይ የተወሰኑ የስራ ክርክሮች 4 ናቸው።

### 3.5.5.3. ስርዓተ ጾታ እና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ አገልግሎት ማጠናከር

ሴት ሰራተኞች ወደ አመራርና ውሳኔ ሰጭነት ለማምጣት ያሉ ማነቆዎችን በመለየት፣ በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ የአመራር ሰጭነት ላይ የሴቶችን ተሳትፎ በትምህርት ደረጃ ያለውን ልዩነት ለማጥበብ እንዲቻል ከትምህርት ተቋሚት ጋር የግማሽ ክፍያና የነጻ የትምህርት ዕድል በማፈላለግ በዲግሪ እና በማስተርስ በጠቅላላው 185 ሰራተኞች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል።

ባለፈው በጀት ዓመት ኤጀንሲው ባከናወነው ጥናት መሰረት በኤጀንሲው በውሳኔ ሰጭነት ቦታ ላይ ያሉ የሴቶች ቁጥር በጣም አነስተኛ የነበረ ሲሆን ኤጀንሲው የሴቶችን በውሳኔ ሰጪነት ቦታ ላይ ለማምጣት ሴቶችን ለማብቃት ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። በዚህም መሰረት በውሳኔ ሲጪነት ላይ ያሉ ሴቶች መጠን ከ 9% ወደ 14.6% ደርሷል። እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ 30 ሴት አመራሮችና ከፍተኛ ባለሙያዎች ለ 5 ቀናት በአመራርነትና ውሳኔ ሰጪነት ዙሪያ ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል።

የሴቶች፣ የወጣቶችንና የአካል ጉዳተኞችን ግንዛቤ ሊያሳድጉ የሚችሉና ሴት ሰራተኞች ጤናቸውን እንዲጠብቁ ለማስቻል የማህጸን ጫፍ፣ የጡት ካንሰርና ስለአካል ጉዳተኞች በተመለከተ 3 ዓይነት ብሮሸሮች ተዘጋጅተው ለሰራተኞች እንዲሰራጭ ተደርጓል። እንዲሁም በሴቶች ፎረም አማካኝነት ኤች አይ ቪ በደማቸው ለሚገኙና የጡት ካንሰር ህሙማን ለሆኑ የኤጀንሲው 3 ሰራተኞች በየወሩ የ 200 ብር ድጋፍ እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል።
በኤጀንሲው የወጣቶች ቀን ተከብሯል። በክብረ በዓሉ ላይ 70 ሰራተኞች የደም ልገሳ አድርገዋል። 470 ችግኞች ተተክለዋል። እንዲሁም ከደም ባንክና ከስኳር ህመምተኞች ማህበር ጋር በመተባበር 51 ሰራተኞች የደም ልገሳና 167 ሰራተኞች የስኳር ህመም ምርመራ በማድረግ በዓሉ እንዲከበር የተደረገ ሲሆን ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ የቅድመ ካንሰር ምርመራ አገልግሎት ክፍል ጋር በመተባበር የጡት ቅድመ ካንሰር ምርመራ እና የማህጸን ጫፍ ቅድመ ካንሰር ምርመራ በሁለት ዙር ለ 36 ሴት ሰራተኞች እንዲመረመሩ ተድርጓል። እንዲሁም ለ 50 ወጣቶች በጤና ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

በኮልፌ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም ውስጥ ለሚገኙ ወላጅ አልባ ለሆኑ ህጻናት ብር 3710 የሚያወጣ የትምህርት መሳሪያና አንድ ኩንታል አልባሳት በቦታው በመገኘት ለ 2011 የትምህርት ዘመን የሚሆን ድጋፍ ተደርጓል።

## 4. የበጀት ዓመቱ የፋይናንስ አጠቃቀም

| ተ.ቁ. | የበጀቱ ርዕስ | በበጀት ዓመቱ የተመደበ የገንዘብ መጠን (በብር) | በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ የዋለ የገንዘብ መጠን (በብር) | በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ የዋለው የገንዘብ መጠን ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር (በ%) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመደበኛ በጀት የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዥ | 2,500,000,000.00 | 3,226,260,735.25 | 129 |
| 2 | የጤና ፕሮግራም መድሃኒትና የህክምና መገልገያዎች ግዥ | 5,589,243,290.00 | 1,548,797,176.58 | 28 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | የስርጭትና አስተዳደራዊ ወጪዎች | 458,065,224.00 | 267,819,352.41 | 58 |
| 4 | የካፒታል ወጪዎች | 750,630,000.00 | 275,700,119.99 | 37 |
| 5 | የአቅም ግንባታ ወጪዎች | 97,079,890.00 | 25,989,036.90 | 27 |
| ጠቅላላ ድምር | | **9,395,018,404.00** | **5,344,566,421.13** | **57** |

**5.** <u>በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎችና ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

<u>ጠንካራ ጎኖች</u>

- የፕሌስመንት ጨረታ ምዘናና የኮንትራት ዝግጅት ሂደት መጠናቀቁ፤
- የክምችት ይዘት ሪፖርትና ትንተና በየወሩ እየተሰራ አስፈላጊ እርምጃዎች መወሰዳቸው፤
- ከአቅራቢዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ችግር ፈች ምክክሮች መደረጋቸው፤
- የፈጣን ለውጥ አምጪ ስልትን በመጠቀም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሆስፒታሎች ላይ የመድሃኒት አቅርቦት መሻሻሉ፤
- ዘመናዊ የተሽከርካሪ ስምሪት መቆጣጠሪያ መሳሪያ (GPS) በተሽከርካሪዎች ላይ መገጠሙ፤

<u>ያጋጠሙ ችግሮች</u>

- የሃገር ውስጥ አቅራቢዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች አለማቅረባቸው፤
- ከዋናው መስሪያ ቤት ወደ ተለያዩ ጤና ተቋማት ለሚላኩ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ሞዴል-19 በጊዜ አለመምጣቱ፤
- የተሰብሳቢ ሂሳብ በወቅቱ አለመሰብሰቡ፤

<u>የመፍትሔ እርምጃዎች</u>

- ሞዴል 19 በወቅቱ ለመሰብሰብ ጥብቅ ክትትል እየተደረገ ይገኛል።
- ከአቅራቢዎችና ወኪሎቻቸው ጋር የጋራ የምክክር መድረክ በማካሄድ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

<u>ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

- የማዕቀፍ ግዥን ማጠናከር፤
- የህይወት አድንና የመሰረታዊ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን አቅርቦት ማሻሻል፤
- ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር፣ የሰራተኞች እርካታ ከፍ ማድረግ፤
- ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት (Enterprise Resource Planning) መዘርጋት፤
- አቅራቢዎችን በመከታተል መድሃኒቶች በሚፈለጉበት ጊዜ እንዲቀርቡ ማድረግ፤